የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ — ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 37
ADDIS ABABA - 13th May, 1997

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸፬/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ..................... ገጽ ፭፻፲፰

CONTENTS

Proclamation No 74/1997

Ethiopian News Agency Establishment (Amendment) Proclamation ..................... Page 518

## አዋጅ ቁጥር ፸፬/፲፱፻፹፱
## የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ“ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፸፬/፲፱፻፹፱ ” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፹፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· ከአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፭) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተጨምሯል፤

“፮· የድርጅቱን ጋዜጠኞችና የቴክኒክ ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል፣ የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ ያወጣል።”

፪· የአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፮)፣(፯) እና (፰) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፯)፣ (፰) እና (፱) ሆነዋል።

፫· የአንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፫(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫(ለ) ተተክቷል፤

“(ለ) ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ጋዜጠኞችንና የቴክኒክ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ደመወዝና አበላቸውንም ይወስናል። የድርጅቱን ሌሎች ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል።”

## PROCLAMATION NO. 74/1997
## A PROCLAMATION TO AMEND THE ETHIOPIAN NEWS AGENCY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Ethiopian News Agency Establishment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the " Ethiopian News Agency Establishment (Amendment) Proclamation NO. 74/1997."

2. *Amendment*

   The Ethiopian News Agency Establishment Proclamation No.115/1995 is amended as follows:

   1) The following new sub-Article (6) is added after sub-Article (5) of Article 8;

      "6) issue directives on the salary scale, employment and administration of journalists as well as the technical staff of the Agency."

   2) Sub-Articles (6), (7) and (8) of Article 8 are renumbered as sub-Articles (7), (8) and (9), respectively.

   3) Sub-Article (3) (b) of Article 10 is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article (3) (b):

      "(b) employ and administer as well as fix the salaries and allowances of journalists and the technical staff in accordance with the directives issued by the Board; employ and administer the other staff of the Agency in accordance with federal civil service laws."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 13th day of May, 1997.

Done at Addis Ababa, this 13th day of May, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING PRESS